# የኢትዮጵያውያን ማኅበራት በውጭ አገር

## ክፍል አንድ፡ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲና ፖለቲካ

ኢትዮጵያውያን ከሁለት በላይ ከሆንና ከአስራ አምስት ደቂቃ በላይ አብረን ካወጋን ወደ ሀገራችን ጉዳይ ዘው እንላለን። ለቅሶም ላይ ይሁን የሰርግ አዳራሽ፣ ቡናም ይጠጣ ቢራ ስለሀገራችን በጣም በመቆርቆር እናወራለን። የምናወራው ሁሉ እውነት ከሆንና ይህም በተግባር ታግዞ ቢሆን ለዘመናት የጉልበተኛና ቀጣፊ መጫወቻ ልንሆን አይገባንም ነበር። እንዲያም ሆኖ ግን ብቅ ብቅ እያሉ መስዋዕትነት እየከፈሉ ያለፉ በርካታ ናቸው። ያልተጣመረው ምኞትና ተግባራችን ግን ችግርና አደጋ ላይ እየጣለን ነው። እንዲያው ምናልባት ስለሀገር ማውራት የምንገደደው ከአየሩ ንብረት፣ ከቤተሰባችንና ከኑሮ ውድነት ባሻገር ሌላ የምንጋራውና በቀላሉ የምንወያይበት ርዕሰ ጉዳይ ስለሌለ ይሆን? ጣቶቻችንን ወደ ሌሎች መቀሰር መውቀስ፣ መክሰስና መፍረድ ከወቀሳ ነጻ ያደርገናል ብለን ስለምናስብ ይሆን? ሁላችንም ስለመተባበር እናወራለን የለመድነው ግን ተጓትተን መውደቅ ከሆነ ከትብብር በፊት ስለሚያስተባብሩንና ወደ አንድነት ስለሚወስዱን ጉዳዮች መነጋገሩ አስፈላጊ ሳይሆን ይቀራል? በዚህ መንደርደርያ ለዛሬው ወዳሰብኩት ጉዳይ ልግባ። እኔም እንደማኅበረሰቡ አባል ከወሬ በላይ እልፍ ያለ ነገር የፈጸምኩ አይደለሁምና ከብዙዎቻችሁ ጋር አብረን ነን። ለውጥ ሊመጣ ይገባዋል የምንል ከሆነ ግን መጀመርያ መለወጥ እንዳለብን አምናለሁ። ቢያንስ በአካል ተቃቅፈን የምንሳሳመውን ያህል በሀሳብ ሳንነካከስ በመደማመጥና በመከባበር ልዩነታችንን አቻችለን ልንጓዝ የምንችልበትን ባህል እንዴት ማዳበር እንዳለብን ጥርጊያውን ብናበጅ መልካም ይሆናል።

ምናልባት የሀገር ፍቅር ወይም ነጻነት ምን ማለት እንደሆነ ተተርጉሞ እንደገና የጋራ ግንዛቤ ካልተገኘለት በቀር የኢትዮጵያውያን ማኅበራት እንደብዛታችንና በየማዕዘናቱ እንደ መበተናችን ተግባራችን ግልጽና ጠንካራ አልሆነም። በተሳሳተ መሰረት ላይ ከመቆም ደግሞ ወይ መበተን ወይም የጋራ ግንዛቤ በአላቸው ሰዎች አማካይነት ጠንካራ ማህበር መስርቶ ከይሉኝታ፣ ከአሉባልታ፣ ከፍርሀትና ከሀሜት በላይ በማሰብ በየምንኖርባቸው ሀገራት ውስጥ የሚገጥሙንን የተለያዩ ችግሮች በጋራ ለመፍታትና የመልካም አጋጣሚዎችም ተጠቃሚ ለመሆን መተባበር ሲሆን፤ እንደ ኢትዮጵያዊነታችን ደግሞ ማህበራትን የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ክንፍ ወይም የአንድ አካባቢ ልጆች ማኅበር ማድረግ ሳይሆን ሀይማኖታችንና አመለካከታችንን እንደያዝን አንድ በሚያደርጉን የኢትዮጵያን ሕዝብ ነጻነት፣ እኩልነት፣ እድገትና አንድነት ዙርያ መደራጀት ማለት ይመስለኛል። በነኒህ ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ መድረስ ከተቻለ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ እጅግ ጠንካራ ይሆናል። ነገር ግን ብዙ አገራት ውስጥ የሚገኙ ማኅበራት በውስጣቸው ብዙ መቋሰል ያለበት ከሚያግባቡ ይልቅ አፍራሽ የሆኑ ጉዳዮች እየበዙ ሊያደርጉ የሚችሉትን እርስ በእርስ የመተጋገዝና የመረዳዳት ተግባር እንኳ ማድረግ ሲሳናቸው ይስተዋላል። ለዚህ ምክንያት ይሆናሉ የምላቸውን የተለያዩ ጉዳዮች በማንሳት የበኩሌን አስተያየት ለመስጠት እወዳለሁ። ለዛሬው የኢትዮጵያ ኮሙኒቲና ፖለቲካ ላይ ላተኩር።

**ብዙዎች የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ከፖለቲካ ነጻ መሆን አለበት ይላሉ፡-** ፖለቲካ አሉባልታ፣ ወሬ፣ ሸርና ደባ ከሆነ በእርግጥም የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ከፖለቲካ የጸዳ መሆን አለበት። ምክንያቱም አብዛኛዎቻችንን የሚበትነን አሉባልታና መሰሪነት ነውና። እንደ እኔ መረዳት ፖለቲካ የማኅበረሰባችንን አብሮነት የሚያስተሳስር የእምነት ወይም የአመለካከት መንገድ ነው። በዚህም ምክንያት ማንም ከፖለቲካ ነጻ ሊሆን አይቻለውም። ነገር ግን በተደጋጋሚ የተመለከትናቸው ጥፋቶችና በደሎች የተፈጸሙት ፖለቲከኞች በምንላቸው ፖለቲካ በዞረበት ያልዞሩ ግብዞችና ጀብደኞች ባስከተሉትና በሚያስከትሉት ቀውስ

ምክንያት በማዘናችን ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ሜዳውን ለቀንላቸው እንዲፈነጩበት በመፍቀዳችንም ሊሆን ይችላል።

ወደ ዋናው ጉዳዬ ከመግባቴ በፊት ግን አንድ እውነት የሚመስለኝን ነገር መናገር እፈልጋለሁ። ምናልባት የሂሳቡን ጉዳይ በትክክል ባልሰራው ከ 75% ያላነሰው በውጭ አገር የሚኖር ነዋሪ በጥገኝነት ፈረንጅ አገር የቀረ ነው። አሁን ወደምንኖርባቸው ሀገራት በቀጥታም ይሁን በአጎራባች አገሮች አድርገን የወጣን በትምህርት ወይም በቤተሰብ መገናኘት አማካይነት ያልመጣን ከሆነ ብዙዎቻችን የፖለቲካ ስደተኞች ነን። ከተለያየ የሀይማኖት መሪዎችና አማኞች ጭምር ፋይላቸውን መልሰው ቢያጤኑት የወጡት በፖለቲካ ጉዳይ ነው። በነጻነት ለማምለክ ካለመቻል አንስቶ እስከሚታወቁት የፖለቲካ ምክንያቶች ጭምር የዛሬው ኑሮአችን በቀጥታ ከፖለቲካ ጋር የተያያዘ ይሆናል። ዛሬ ፖለቲካ ፈጽሞ አያዋጣምገባንም የምንልና ነገር ግን በዚህ ስበብ ወደ ነጻ ምድር የመጣን ሰዎች ቢያንስ የህሊና እዳ አለብን!! በፖለቲካው ትግል ምክንያት በታሰሩ በተጋዙና በተገደሉ ሰዎች ጫንቃ ላይ ተሸጋግረን የወጣን ሰዎች ፖለቲካን በሩቁ ብንል ቢያንስ መዋሸታችንን ለራሳችን ልብ ልንለው ይገባል። እስኪ ለውይይት እንዲመች አንዳንድ ነጥቦችን ለመዘርዘር ልሞክር።

ይህን በተመለከተ ብዙዎቻችንን ሊያግባባን በሚችል መልኩ ከዚህ ቀጥሎ የኢትዮጵያውያን ማኅበራት ከፖለቲካ ነጻ ሊሆኑ የማይችሉባቸውን ነጥቦች ልዘርዝር፡-

- በነጻነት ማሰብ፣ መናገርና መስራት የምንደግፈው ከሆነ ይህን ነጻነት ያገኙ ዘንድ ለሚታገሉ የሰው ልጆች በሙሉ ድጋፍ መስጠት ሰብዓዊ ግዴታ ነው ብለን የምናምን ከሆነ፤
- የሰው ልጅ ወደዚህ አለም ለመምጣት ፈቃዱ ተጠይቆ ከየትኛው ማህበረሰብ መወለድ እንደሚፈልግም አውቆት አይመጣምና ከዚህ ወይም ከዚያኛው ዘር በመወለዱ የተለየ በደል ሲፈጸምበት ትክክል አይደለም የምንል ከሆነ፣
- የሰው ልጅ በችሎታው እንጂ የዚህ ወይም የዚያኛው ፖለቲካ ድርጅት አባል በመሆኑ ብቻ የተለየ የስራ እድል ወይም የኢንቨስትመንት እድል ሊሰጠው አይገባም ብለን የምናምን ከሆነ፤
- የኢትዮጵያን ኮሚኒቲ ስብስብ ስሙንና ቅርጹን የሚሰጠው የኢትዮጵያ ልጅነት ከሆነና የአገሩ ሕልውና አንድነትና ነጻነት የግድ ያገባዋልና በዚህ ጉዳይ ጸንተን መቆም አለብን የምንል ከሆነ፤
- ባህሉ፣ ወጉ፣ ሀይማኖቱ፣ ቋንቋው እንዲጠበቅለት፣ እንዲከበርለትና እንዲያድግለትም ተቀብለን ለዚህም አስተዋጽኦ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለን ካመንን፤
- ህግና ህገ መንግስት እንዲከበር ማንም እንደተመቸው እየሰረዘና እየደለዘ ወይም ያለውን እያጣመመና እያወላገደ ፍትህ ሊያዛባ አይገባውም ብለን የምናምን ከሆነ፤
- እንደየምንኖርበት የሀገር ሁኔታ በኢትዮጵያውያን ላይ በተለይ ወይም በቀለማችን ምክንያት በጠቅላላው ወይም የስደተኛ መብት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተለየና የተነጣጠረ ጥቃት ቢደርስብን ያንን ለመታገል መነሳት አለብን የምንል ከሆነ፤
- በተፈጥሮ ምክንያት የሚከሰቱ እንደ ድርቅ፣ ረሀብ ያሉ ጉዳዮች በሚፈጠሩበት ጊዜ ድጋፍ መስጠት አጣልቶ ባያውቅም። ከዚያ በላይ ደግሞ ብዙ ተሞክሮና እውቀቱ ስለአለን መፍትሄ መጠቆምም አስፈላጊ ነው። የኢትዮጵያ የረሀብ ጉዳይ ከመንግስት የተሳሳተ የመሬት ይዞታ፣ ከኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥና ካለው በዘር ላይ የተመሰረተ አስተዳደር ምክንያት የመጣ ችግር ነው የምንል ከሆነ፤

- እኛ የምንኖርባቸው አብዛኛዎቹ የአውሮፓ፣ የሰሜን አሜሪካና ሌሎችም አገሮች በብዙ ሰዎች የነጻነት ትግል ምክንያት ነው እኛን ማስተናገድ የቻሉትና ከፖለቲካ ትግል ተጠቃሚዎች ከሆንን በዚህ ምክንያት የተገኘው ጥቅማ ጥቅም ሁሉ የፖለቲካ ውጤት ነው። ስለዚህ የፖለቲካው ትግል ባለውለታዎች ወይም ባለእዳዎች መሆናችንን ልብ የምንል ከሆነ።

ከላይ በመጠኑ የገለጽኳቸውንና ሌሎች በርካታ ሁኔታዎችን መመልከት የማይችል የኢትዮጵያውያን ማኅበር እንደ እድር ወይም እቁብ ለየት ያለ አደረጃጀት ያለው ካልሆነ በቀር የኢትዮጵያውያን ማኅበር ተብሎ ሊጠራ እንዴት ይቻለዋል? ኢትዮጵያ ፈራርሳ እስከታልቅ በስምዋ እንሰባሰብ በሚል ግንዛቤ ካልተደራጀን በቀር ሌላ ምን ልንለው እንችላለን? ይህ በሰፊው ውይይት ሊደረግበት የሚገባውና የጋራ ግንዛቤ ልናገኝበት የሚያስፈልግ ጉዳይ ነውና እንደነበረው በመቀጠል ወይስ በተጠናከረ መልክ በመደራጀት እድገት ልናሳይ የምንችል የሚለውን ጥያቄ እንመክርበት ዘንድ ለማሳሰብ ነው። በሚቀጥለው ከዚህ ጋር ተያያዥ ናቸው ብዬ የማምንባቸውን ጉዳዮች አስከትላለሁ እስከዚያው መልካም ቆይታ።

መልካም ጊዜ

ከ ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com
www.ethiomedia.com